# ሠ ቅ ጸ ላ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!



ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ቅጽ: ፩ ቁጥር: ፬ ቀን: ታሕሳስ ፲፱ ፪ሺ፲

በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ

## ወያኔ የሰጠን ምርጫ ባርነትን ወይም ሞትን ነው!

ሟቹ የወያኔው አውራ የነበረውና በሙት መንፈሱ አገሪቱን እንመራታለን የተባለለት መለስ ዜናዊ፣ ለትግሬ-ወያኔ የበላይነት ጠብቆ ለመጓዝ ምን ያህል እንዳጎደለ ከሞቱ በኋላ ባሉት ጥቂት ዓመታት በወያኔዎቹ ፖለቲካዊ አመራር ዙሪያ የሚስተዋለው ድህነት የቱን ያህል የሠፋና የጠለቀ እንደሆነ ከተስተዋለ በኋላ ነው። መለስ ሥልጣኑን የተናዘዘለት እንደሆነ የሚነገርለት ደብረጽዮን ገብረሚካኤል ከዐባይ ወልዱ ያልተሻለ ወደል መሃይም መሆኑን ከጅምሩ እየተስተዋለ ነው። «ጠላት ብርቁ» የሆነው የወቅቱ የትግሬ-ወያኔዎቹ «ራስ» ደብረጽዮን፣ የጎንደርን ሕዝብ እንደ ሕዝብ በጠላትነት ሲፈርጅ፣ ትናንት ምን ነበር? እንዴትስ ነበር? ነገስ ምን ሊያስከትል ይችላል? ብሎ የትናንቱን ከዛሬው፣ የዛሬውን ከነገው አዛምዶ ለማየት አልሞከረም። ትናንትን በቅጡ ያልተረዱ ዛሬን በትክልል ሊያውቁ አይችሉም፣ በዚህም በነርሱ ዘንድ ነገ ጥቅጥቅ ጨለማ ነው። ዛሬ በወያኔ ሠፈር የምናየው መጠላለፍና ዝብርቅርቅ ሁኔታ ከዚህ የታሪክና  የፖለቲካ ድህነት የመነጨ መሆኑን እንገነዘባለን።

ትናንት በአንድ የመንግሥት ነው በተሰኘ ቴሌቪዥን የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ነው የተባለው ኃይለማርያም ደሣለኝ፣ በአገሪቱ ውስጥ ስለተፈጠረው ምስቅልቅል ሁኔታና በምስቅልቅሉ ስለተጎዱ፣ስለተበደሉና ስለተገደሉና  ንፁሕ ዜጎች ተጠያቂው በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ነው በማለት በገለጸበት የደቂቃዎች ልዩነት ውስጥ፣ አዲሱ የወያኔው ሊቀመንበር በዚያው ቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብሎ፣ «በርካታ ጠላቶች ተነስተውብናል፤ እነኚህን ፀረ-ሰላምና ፀረ-ልማት ኃይሎች የማያዳግም ትምህርት እንሰጣቸዋለን» ሲል መሰማቱ የቱን ያህል ሕዝቡን እንደናቀና ሊጨርሰውም እንደተዘጋጀ በግልጽ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ፣ በአመራሩ መካከል አንድነት የሚባል ነገር የሌለ መሆኑን ያሳያል። በአገሪቱ ላይ የሰፈነው አመራር አንድ ወይስ ሁለት? ወይስ ሁለቱም የአንድ መንግሥት ሁለት ገጽታዎች ናቸው ብሎ ለመጠየቅ መንገድ ይመራል። የነዚህ አንድነትና ልዩነት፣ አባቶቻችን እንደሚሉት ፤«ሸልም እንደሆን ይገፋል፣ዱባም ከሆነ ይጠፋል» ማለትን እንመርጣለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በረጅም ታሪኩ በትግሬ-ወያኔዎች የደረሰበት ዓይነት ንቀት፣ ውርድት፣ ግፍ፣ ስደትና መከራ አይቶ አያውቅም። ኅልውናውም ሆነ አብሮነቱ እንደዚህ ተሸርሽሮና ርስ በራሱ ተፈራርቶ አያውቅም። ለዚህ ደግሞ ከትግራይ ሕዝብ ውጭ ሌላ ምስክር ሊያስቆጥር የሚችል አይደለም። ማንም የኢትዮጵያን ታሪክ በቅጡ የተገነዘበ ሰው ሊገነዘበው እንደሚችለው፣ የትግራይ ክፍለሀገር ተፈጥሮአዊ አቀማመጡ በቀይ ባሕር ዳርቻ  ላይ በመሆኑ፣የጠላትም ሆነ የወዳጅ መግቢያና መውጫ በር ነው። የአገሪቱ ጠላቶች ደጋግመው የመጡት በዚሁ በር ነው። በመሆኑም ሕዝቡ እንደ ሕዝብ ለአገሪቱ አንድነትና ነፃነት ከሌሎች ነገዶችና ጎሣዎች ቀድሞ በመቆም ከከፈለው ሁለንተናዊ መስዋዕትነት በተጨማሪ፣ ተፈጥሮአዊ አሠፋፈሩ የገፈቱ ግንባር ቀደም ቀማሽ እንዲሆን ያስገደደው በመሆኑ ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት ከፍተኛ ዋጋ ሲከፍል የኖረ ሕዝብ መሆኑ በግልጽ ይታወቃል። እስከ ወያኔ ውልደት ድረስ የትግራይ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱና በአንድነት ወዳድነቱ ጥያቄ ውስጥ ወድቆ የማያውቅ ጀግና ሕዝብ መሆኑን የእንትጮ፣ የደባርዋ፣ የድሆኖ፣ የጉራ፣ የጉንደት፣ የገላባት፣ የመተማ፣ የዐድዋ ጦርነት አውድማዎች ጥለው የወደቁ የትግራይ ጀግኖች አፍ አውጥተው የሚመሰክሩት ሐቅ ነው። ጠላቶቻችን በተደጋጋሚ በዚህ በር በኩል ለመግባት ሲጥሩ፣ የትግራይ ሕዝብ ቀድሞ የበሩ ዘብ በመሆን ለሚያሰማው የወገን ጥሪ ሌሎች ነገዶች በተላይም የዐማራና የኦሮሞ ሕዝብ ፈጥነው በመድረስ የሁሉም ኢትዮጵያውያን መታወቂያ እና የወል ቤት የሆነችውን አገር ከተስፋፊዎችና ቅኝ ገዥዎች ቁጥጥር ሥር እንዳትወድቅ ወሳኝ ሚና መጫዎታቸው ግልጽ ነው።

በእነዚህ የአገር ዋልታና  ማገር ሆነው፣ ልዩነቶቻቸውን ጌጦቻቸውና ውበታቸው አድርገው ሰምና ፈትል ሆነው የኖሩ የትግሬ፣ የዐማራ እና የኦሮሞ ነገዶችን ነጣጥሎ፣ አጥፊና ጠፊ በማስመሰል በሚያራምደው የዘር ፖለቲካ፣ የሕዝቡን የኢትዮጵያዊነት እና የአብሮነት ስሜት የቱን ያህል እንደሸረሸረው በግልጽ ይታወቃል። ወያኔ ሆን ብሎ ያራገበው የዘር ፖለቲካ፣ ለሕዝቡ ቁሣዊ ሕይዎት ላይ ጠብ የሚል ነገር ሊያመጣ ባለመቻሉ፣ ወደነበረ አንድነቱና አብሮነቱ መመለስ የተሻለ እንደሚሆን ከተሞክሮው በመገንዘብ፣ በወያኔ አገዛዝ ላይ ጀርባ መስጠት መጀመሩ የትግሬ-ወያኔውን አመራር ቀልብ ነስቶታል። በመሆኑም በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት ነገድና ጎሣዎች በሕዝብ ብዛት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን የዐማራና የኦሮሞ ነገዶች እሳትና ጭድ አድርጎ የአገዛዙን ዕድሜ ለማራዘም የተለያዩ የመከፋፈያ ዘዴዎችን ሲጠቀም እየተስተዋለ ነው። የዐማራውና የኦሮሞው ነገዶች ወደ ጥንተ ጥዋቱ አንድነታቸው የመመለስ ጉዳይ እንቅልፍ የነሳው ደብረጽዮን፣በሁለቱ ነገዶች ላይ የጥፋት እጁን አንስቷል። በደማችን ከደርግ እጅ ፈልቅቀን በማውጣት በመዳፋችን ያስገባናትን ሥልጣን አንለቅም፣ ሥልጣን የሚገባው ለትግሬ-ወያኔ ብቻ ነው፣ በመሆኑም  በአገዛዛችን ላይ ያመጸውን ሕዝብ ፀጥ ለማሰኘት የማንፈነቅለው ደጋይ አይኖርም እያለን ነው።

ትዕግሥትን እንደፍርሃት፣ ማስተዋልን እንደ ሞኝነት፣ከጠብ ይልቅ ለፍቅር ሕዝቡ መምረጡና ሁሉንም ነገር ጊዜ ሊፈታው ይችላል ብሎ በአስተዋይነት መመልከቱ ለበለጠ ጥቃትና ችግር እየዳረገው መምጣቱን ሕዝባችን በሂደት እያስተዋለው መጥቷል። ይህም የግፍ ጽዋው ሞልቶ መፍሰስ በመጀመሩ፣ ሕዝቡ የግፍ አገዛዝ ይብቃ! አሻፈረኝ፣ ከእንግዲህ ለትግሬ-ወያኔ አልገዛም በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ በሚያስተጋባበት በአሁኑ ሰዓት፣ እንደተለመደው በኃይል ረግጠን እንገዛለን በሚል ትዕቢትና እብሪት የአፈናና የግድያ ሥልት ለመቀየስ መቀሌ ላይ የሤራ ድሮችን ሸርበው በአዲስ ወኔ ተነስተዋል።

ለዚህ ዓይነቱ ሤራ የገፋፋቸውም «እሳትና ጭድ አድርገናቸዋል» ያሏቸው የኦሮሞና የዐማራ ነገዶች ፊታውራሪ ሆነው በራሱ በወያኔ የተሾሙት ጉጅሌዎች፣ የሕዝቡን ድምፅ በመስማት፣የታሪክ ተጠያቂም ላለመሆን ከወያኔ ፍላጎት አፈንግጠው ለሕዝብ ጥያቄ ጆሮ መስጠት መጀመራቸው ያሳደረባቸው የጥፋት ከበባ ክብደት እንደሆነ ይታመናል። የኦሮሞና የዐማራው ሕዝብ አንድነትና በጋራ፣ ለጋራ ብሔራዊ ጥቅምና አገራዊ አንድነት መቆም፣ ለወያኔው አመራር ፣ከሁሉም በላይ ለዐድዋው ቡድን የውስጥ እግር እሳት ሆኖበታል። የታሪክ፣ የባህልና የፖለቲካ  ዕውቀት ድህነታቸው የቱን ያህል ጥልቅ እንደሆነ ማሳያው፣የዐማራና የኦሮሞ ነገዶች እንደ ሰርገኛ ጤፍ የተቀላቀለ፣ እንደ ውኃና ወተት የተዋሐደ መሆኑን ባለማወቅ፣«ዐማራውና ኦሮሞው በምንም ተዓምር አንድ ሊሆኑ አይችሉም፣ እሳትና ጭድ አድርገናቸዋል» ብለው ደፍረው በአደባባይ ለመናገር የደረሱ ጉዶች ናቸው። የዚህ ዓይነቱ ተራ ነገር በአባይ ፀሐዬ፣ በሥብሃት ነጋ፣በዐባይ ወልዱ፣ በሣሞራ የኑስ እና በደብረጽዮን ዓይነት የትግሬ-ወያኔ ቡድን አውራ ነን ከሚሉ ጉዶች ሲነገር መስማት፣ የትግሬ-ወያኔዎቹ ቡድን ሕዝብ ለመምራት ቀርቶ ከብት ጠብቆ ለመግባት ችሎታ የሌላቸው የባለጌዎች ስብስብ መሆኑ፣ ለራሱ ለትግራይ ሕዝብ ውርደት ነው። እነዚህም ናቸው ኩሩውንና ጀግናውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ለዘላለም እንግዛ የሚሉት።

እነዚህ ወገኖች ያላወቁት ነገር፣እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ያለ አስተዋይና በሳል ሕዝብ በእንደነዚህ ያሉ ስግብግቦች፣ ከሐዲዎች፣ አገር ሻጮችና  የአንድ መንደር ስብስቦች «ባርያ» ሆኖ ለዘላለም ሊገዛ የማይችል እንደሆነ መገንዘብ አለመቻላቸው ነው። የዐማራና የኦሮሞን ነገዶችን የጠነከረ አንድነትና የአብሮነት ስሜት ያቃለሉ መስሏቸው፣ ሆድ አደር የሆኑ ሰዎችን ስብሰብ ይዘው ጎንደር መግባታቸው የአስተሳሰብ ድህነታቸውን በይፋ ያጋለጠ ክስተት ሆኗል። ትናንት ሳይጠሩዋቸው አቤት እና ወዴት ይሏቸው የነበሩት ወዶገባ አሽከሮቻቸው ጀርባቸውን ሰጥተው ጆሮአቸውን ሲነሷቸው ምን አስበው እንደሆን ሊገነዘቡ አለመቻላቸውን ታዝበናል። የለማ መገርሳና የገዱ አንዳርጋቸው ከወያኔ ፍላጎት የማፈንገጥ ጉዳይ  የመነጨው፣ ባለፉት 26 የትግሬ ወያኔ አገዛዝ በኦሮሞና በዐማራ ሕዝብ ላይ የተፈጸመው ዞሪያገባ ግፍና መከራ ጽዋ ሞልቶ መፍሰስ ካሳደረባቸው ወገናዊ ስሜት መሆኑን ስተውታል። ለማ እንዳለውም «እኔ የኦሮሞ ሕዝብ አሽከር እንጂ፣ የወያኔ ጀሌ አይደለሁም» ማለቱን ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ በቅጡ ሊረዳቸው አልቻለም። ወይም ሊረዱት አልፈለጉም።

እነዚህ የትግሬ-ወያኔ ቁንጮ ነን የሚሉ ሰዎች ድህነት፣ ችግርና ውርደት ካሳደረባቸው ተጽዕኖ በተጨማሪ፣ በድንገት የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዥ መሆናቸው እሳና ይሉኝታ የሚባሉትን መልካም ዕሴቶች የገፈፋቸው በመሆኑ፣ ዓይን ላወጣ ስግብግብነት እና ሁሉንም ነገር ለእኛ እንዲሉ የልብ ልብ ሰጥቷቸዋል። ይህም በመሆኑ፣ የትግራይን ሕዝብ ጋሻና ጦራቸው አድርገው በዐማራውና በኦሮሞው ነገዶች ላይ የጥፋት ክንዳቸው ላይዝል ከበሮ እየደለቁ ነው። ይህ ድለቃ እንደጨው ዘር በመላ አገሪቱ በገዥነትና በሰላይነት የተሰራጨውን የትግሬ ትውልድ ለመከራ እየዳረጉት እንደሆነ ያስተዋሉት አይመስልም። ከዚህ ላይ ችኩልነት፣ ትዕቢትና ማንአህሎኝነት መለያው በሆነ ማኅበረሰብ፣ ይህ ዓይነቱ የጦርነት አዋጅ ለከፍተኛ መከራ የሚዳርግ እንደሆነ የነገዱ አባሎች ሊያስቡበት ይገባል። ዛሬ ኦሮሞውም ሆነ ዐማራው ወገኔ ከሚሏቸው ቡድኖችና አመራሮች ጎን በነቂስ መቆሙ ይስተዋላል። እነዚህን ሕዝቡ የኔ ናቸው የሚላቸውን ቡድኖችና ግለሰቦች መነካካት በእሳት መጫወት እንደሆነ ወያኔና አፍቃሪ ወያኔ የሆኑ ሁሉ ግልጽ ሊሆንላቸው ይገባል።

ወያኔ ለ17 ዓመታት በየበረሃው የዶለቱት እና የመከሩበት አጀንዳና የትግል ጉዞ ከዛሬው የሥልጣን ማማ ላይ እንዳደረሰው ይታወቃል። ከዚህ በኋላ ባለፈው ሁለት ወር አይደለም እንደገና 17 ዓመት ቢዶሉትና ቢመከሩ የታቻምናውንና ያምናውን ፈረስ መጋለብ አይቻላቸውም። አገዛዙ የገባበት የንቅዘት ማጥ ስፋትና ጥልቀት በአባላቱ መካከል የድሮውን ዓይነት መከባበርና መተማመን መልሶ ሊፈጥር የሚያስችል አይደለም። ከሁሉም በላይ አውራጃዊ ልዩነቱ በሥልጣን አያያዝና በሀብት ቅርምት ጎልቶ የወጣ በመሆኑ፣ ማን ከማን ያንሳል የሚለው የመጠፋፋት ፍክክር በአባላቱ ውስጥ ሰርጿል።

ለጉዳይ አስፈጻሚነት ወያኔ ያደራጃቸው የኢሕአዴግ እህት ድርጅቶች ፣ እኛስ ከማን እናንሳለን? የሚል ጥያቄ ከማንሳት ዘለው፣ ወያኔን በግልጽ መጋፋት ይዘዋል። ይህም «ብርሌ ከነቃ ፣አይሆንም ዕቃ» ነውና ወያኔ በየትኛውም መልኩ ቢሆን፣ ከእንግዲህ ርስ በራሱ ከመጠፋፋት ውጭ ራሱን አደራጅቶ የሕዝቡን መነሳሳት ሊገታ

የሚችልበት ቁመና የለውም። የወያኔ አመራርና ስብሰብ ትንሽም ብትሆን፣ የማስተዋል እንጥፍጣፊ ካላቸው ብቸኛው አቋራጩና ተመራጩ መንገድ ከወጣበት የሥልጣን ማማ ላይ ወርዶ፣ ሥልጣኑን ለሕዝብ ማስረከብና የትግራይ ሕዝብ ከተጠያቂነት ማዳን ነው። ይህን ካላደረገ ራሱም ሆነ ማኅበራዊ መሠረቴ ነው ለሚለው የትግራይ ሕዝብ የሚጠብቀው መከራ የከፋ ሊሆን እንደሚችል መገመት ክፉ አሳቢ መሆን አይደለም። መጭውን በአግባቡ መገንዘብ እንጂ!

ለረጅም ጊዜ የተካሄደው የወያኔ የመቀሌ ስብሰባ ሕዝቡ እንደጠበቀው ለተነሱ ሕዝባዊ ጥያቄዎች ማለትም፣«የወያኔ አምባገነንነት ይቁም!»፤ «በሕዝቡ ላይ የታወጀው የእልቂት አዋጅ ይነሳ!» «የአገሪቱና የሕዝቡ ሀብትና ንብረት መዘረፍ ይብቃ!»፤ ወዘተ ለሚሉት ጥያቄዎች ምንም ዓይነት መልስ ሳይሰጥ ተነስቷል። እንዲያውም የስብሰባው ዋነኛ አጀንዳ ከላይ የተጠቀሱት የሕዝብ ጥያቄዎች ሳይሆኑ፣ «የተነሱብንን ጠላቶች እንዴት ማጥፋት እንችላለን?» የሚል እንደነበር በወያኔው አዲሱ ሊቀመንበር በኩል ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲገለጽ መደረጉን የሰማነው በታላቅ ትዝብት ነው። ይህ የመቀሌ ስብሰባ ውሳኔ በኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ቀርቦ፣ ለአፈጻጸም አወዛጋቢ ሆኖ በመገኘቱ፣ ጠላት ተብለው የተፈረጁት ወገኖች ተቆርቋሪዎች ስብሰባውን ረግጠው እንዲወጡ ምክንያት መሆኑ ታውቋል።

ይህ በእንዲህ እያለ፣ ወያኔ በተለመደ ከፋፋይ ሤራው፣ በሶማሌና በኦሮሞ ነገዶች መካከል ራሱ የፈጠረውን ቅራኔ ለማባባስ የተለያዩ ደባዎችን እየሸረበ ነው። ለዚህም በላፈው ሳምንት 18 ኦሮሞዎችና ከሰላሳ ያላነሱ ሶማሊዎች፣ የሲቭል ልብስ በለበሱ የፌደራል ፖሊሶች አሰማርቶ አሰቃቂ ግድያ እንዲፈጸምባቸው ተደርጓል። ይህ በሶማሌዎች ነገድ አባሎች ላይ የተፈጸመ የግፍ ግድያ ዋና ዒላማ ለማ መገርሳን የወንጀሉ ተጠያቂ አድርጎ ከያዘው ኃላፊነት በማንሳት እንደነ ታምራት ላይኔ እና መላኩ ፋንታ በእስር ለማሰቃየት የታቀደ የወያኔ የተለመደ ተጠቅሞ የመወርወር ተንኮል መሆኑ ተደርሶበታል። ይህ ሲታወቅበት፣ «የኢየሱስ በግ» የሆነውን ጠቅላ ሚኒስትር ተብየውን ኃይለማርያም ደሳለኝን ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተማጽኖ ንግግር እንዲያደርግ ጽፈው የሰጡትን እንዲያነብ ያስገድዱታል። ወያኔ በኃይለማርያም ደሳለኝ በኩል የተማጽኖ መግለጫ እንዲሰጥ ሲያደርግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔው አፍለኛው መሪ፣ ደብረጽዮን «ጠላቶቻችን ከምንጊዜውም በላይ ተነስተውብናልና፣ እንደ ሕዝብ ከምድር ገጽ ከመጥፋታችን በፊት ጠላቶቻችንን መቅደም ይጠበቅብናል» በማለት ለወያኔ አባሎችና ለትግራይ ሕዝብ የተነሱ ተጠቃን ጥሪ አድርጓል።

ይህ በደብረጽዮ በኩል የቀረበ የትግራይ ሕዝብ የወያኔ ባሕር፣ የጥፋት ተባባሪና ደጋፊ ሆኖ እንዲቀጥል የተደረገ ጥሪ፣የአጥፍቶ መጥፋት ድግስ መሆኑን ሕዝቡ አውቆ የጥፋቱ ተባባሪ ከመሆኑ በፊት ጉዳዩን በቅጡ ሊረዳው ይገባል እንላለን። ጥቂት የሥልጣን ናፋቂዎች ከትግራይ ሕዝብ ተወለድን እና የርሱም ወኪሎች ነን የሚሉ እጃቸው በንፁሀን ደም የጨቀዩና የአገር ሀብት ዘርፈው ያልጠረቁ ወያኔዎች ከገቡበት ማጥና በላያቸው ላይ ካንዣበበው የሞት ጥላ ለማምለጥ ሲሉ የትግራይን ሕዝብ ጋሻና ጦራቸው ለማድረግ ለከፈቱት ፕሮፓጋንዳ ሰለባ እንዳይሆን ደጋግሞ ሊያስበበት ይገባል እንላለን።

ደብረጽዮን ጠላቶቻችን ተነስተውብናል በማለት ለትግራይ ሕዝብና ለወያኔ አባሎች ያስተላለፈው መልክዕት፣ ሕዝቡና አባላቱ፣ በዐማራና በኦሮሞ ነገዶች ላይ ለሚያውጀው የጥፋት አዋጅ፣ ሕዝቡ መመሪያውን ነቅቶ እንዲጠባበቅና ሳይዘገይ ተግባራዊ እንዲያደርገው የሚያዝ መሆኑ ጥርጥር የለውም። በዚህ ረገድ ወያኔ ጠላት ለማፍራት ችግር የሌለበት ድርጅት መሆኑ ይታወቃል። ለምን? እንዴት? መቸና የት? ብለው የሚጠይቁ ሁሉ የወያኔ ጠላቶች ናቸው። ትናንትም ዛሬም ትምክህተኛው ዐማራ፣ ጠባቡ ኦነግ፣ እንደሚል ሁሉ፣ ዛሬ ወይም ነገ ጠባቡ ኦሕዴድ፣ ትምክህተኛው ብአዴን ፣ዘላኑ ሶማሊያ ሊል የማይችልበት ምክንያት አይኖርም።

ያለፉትን 44 የወያኔ የትግልና የሥልጣን ዘመኖች በቅጡ ስንመረምር፣ የትግራይ ሕዝብ የወያኔ ባሕር፣ ዓይንና ጆሮ ሆኖ የዘለቀውን ያህል፣ አሁንም በዐማራና በኦሮሞ ነገዶች ላይ ላቀደው የጥፋት ዘመቻ ተባባሪ መሆን አይችልም ሊያሰኙ የሚችሉ ተጨባጭ ማስረጃዎች የሉም። ይህም በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያንገሸገሸውን አገዛዝ ለመጣል በሚያደርገው ግብግብ፣ የትግራይ ሕዝብ «ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወገጥ» እንዳይሆንበት በእጅጉ ያሳስበዋል። ይህን መሠረት የያዘ ሥጋት የትግራይ ሕዝብ አውቆ፣ ጊዜው ሳይዘገይ የአሰላለፉን ጎራ በፍጥነት በመለየት፣ ከታሪክና ከኢትዮጵያዊነት ጎን እንዲሰለፍ ጥሪአችን ስናቀርብ በዕውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ስሜትና እምነት ነው።

ማንም በግልጽ እንደሚረዳው፣ ወያኔ የሥልጣን ዘመን ማራዘሚያየ ብሎ የተከተለው ስልት በኦሮሞና በዐማራ ነገዶች መካከል ሰው ሠራሽ ልዩነቶችን በማባዛት ሁለቱን ታላቅ ነገዶች ዓይንና ናጫ በማድረግ ኢትዮጵያዊ የማንነት ዕሴቶችን በማጥፋት ላይ የተመሠረተ ስትራቴጂ ይከተል እንደነበር ይታወቃል። ይህ ስትራቴጂ ግን፣ ጎንደር ላይ «የኦሮሞ ደም ደማችን ነው!» የሚለው ድምፅ ሲሰማና ኦሮሞዎቹም ጎንደር ላይ ለተሰማው ድምፅ የሰጡት አዎንታዊ ድምፅ፣ ወያኔ በኦሮሞና በዐማራ ነገዶች በመካከል ገንብቶት የነበረው የጥላቻ ግንብ በሤራ እንዲለያዩ በተደረጉት ነገዶች የአንድነትና የአብሮነት ድምፅ ተናደ። ይህም ወያኔ በሁለቱ ነገዶች ጥላቻ አፈርሳታለሁ ያላት ኢትዮጵያ ለጊዜውም ቢሆን በዚህ ልዩነት ልትፈር የማትችል እንደሆነ ሤራውን ሕዝቡ አከሸፈበት።

በሌላ በኩል በኦሮሞና በዐማራ መካከል የገነባው የጥላቻ ሤራ መክሸፉን ሲረዳ፤አዲስ የአገር ማፍረሻ ስልት ይዞ መጥቷል። አዲሱ የአገር ማፍረሻ ስልቱም በኦሮሞና በሶማሌዎች መካከል ያሉ ጥቃቅን ልዩነቶችን በማራገብ ወደ ርስ በርስ ግጭቶች እንዲገቡና ሶማሌዎች ከኢትዮጵያ የመገንጠል ጥያቄ እንዲያነሱ የመገፋፋት ጥረት ማድረግ ነው። ይህ ግን ከሶማሊዎቹ ፖለቲካዊ ባህል አንፃር ሲመዘን እስከ ዘለቄታው ከወያኔ ጎን ቆመው ዓላማውን ያሳካሉ ብሎ ለማመን ያስቸግራል። ያም ሆኖ፣ «ጅል ዳኛ የፈረደው ዓመት ያሚግታል» ነውና በዚህ ረገድ በሕዝባችን የአብሮነት ስሜት ላይ ጥላሸት የሚቀባ ተግባር አይፈጽሙም ለማለት አያስደፍርም።

ወያኔ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ሥልጣን ቁጮ ላይ ካልቆየ፣ አገሪቱን ማፈራረስ እንደግቡ ይዞት የቆየ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል። አገሪቱን ለማፈራረስ እንደመሳሪያ እጠቀምባቸዋለሁ ያላቸው በነገዶች መካከል ያሉ ልዩነቶችን የማባዛቱ ተግባር የሚጠበቀውን ያህል ለፍሬ የሚበቃ ሆኖ አልተገኘም። በያዘው መንገድም ብዙ ሊገፋበት የሚያስችለው ሁኔታ የተጣበበ ነው። ሽንፈትን ተቀብሎ ለመኖርም የፈጸሙዋቸው ወንጀሎች ባንድ በኩል፤በሌላ በኩል የእነርሱ ሽንፈትን ያለመቀበል ሁኔታ ስለሚታገሏቸው፣ ያላቸው ብቸኛ አማራጭ የትግራይን ሕዝብ ተገን በማድረግ ትግራይን መገንጠል የሚለው ሁለተውኛውን አማራጫቸውን እንደሚመርጡ ይጠበቃል።

ይህን ለማድረግ ሌላ ዙር የመቀሌ ስብሰባ ሊጠራ ይችል ይሆናል። ወይም ሌላው ዙር ስብሰባ በወያኔው አመራር ውስጥ የተከሰተውን የሰፋ ልዩነት አጉልቶ አደባባይ በማውጣት ሊበታትነን ይችላል በሚል ስጋት፤ለሸሸት በሚያመች ሌላ ቦታ ለመሰባሰብ ሊሞክሩ እንደሚችሉ ይታሰባል። ስብሰባው የትም ይሁኑ የት፣ ከተደረገ የመቀሌው ስብሰባ ወደ ሥልጣን ማማው ያወጣውን የዐድዋ ቡድን የሚቃወም፣ የሕዝቡን ጥያቄ ከመመለስ ውጭ ሌላ አማራጭ መንገድ የለንም የሚል ኃይል የዐድዋውን ስብስብ ገፍትሮ ብቅ ሊል የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል መገመት ይቻላል። ሌላው የወያኔው ቡድን አማራጭ ሊሆን የሚችለው፣ በሚያደርጉት ስብሰባ እንደድሮው ተስማምተውና ኃይል ገዝተው ሊወጡበት የሚያስችላቸው ሁኔታ የተጣበበ በመሆኑ፣ ሁሉም ራሱን ለማውጣት ቀደም አድርጎ ባዘጋጀው የጓሮ በር ለመውጣት እሽቅድምድም ሊገባ ይችላል። ወያኔዎች ከላይ ከተጠቀሱት የቢሆን አማራጮች የትኛውን ሊከተሉ እንደሚችሉ የሚያሳየን ጊዜ ነውና እርሱን መጠበቅ ግድ ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ በጠላትነት ፈርጆና እርሱን እናጠፋለን ብሎ ተነስቶ ካሰበው ይደርሳል ለማለት የሚያስችል በቂ ማሳያ ስለሌለ፣ ወያኔ ባሰበው መልኩ ይሳካል ብሎ ለማመን ብዙ የሚያስኬድ አይሆንም።

ሌላው ክፍት አማራጩ እና አሁን አሁን በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን መሣሪያዎች የሚደመጡ መረጃዎች ከሚሰጡት ፍንጭ በመነሳት፣ ወያኔ ከሻዕቢያ ጋር ባድመን ለቆና፣ ሌላም ካሣ ሰጥቶ የትግራይ ትግርኚ ፕሮጀክትን ሕይዎት እንዲዘራ ለማድረግ ሊሞክር እንደሚችል መገመት አይከፋም። ትግራይን የመገንጠሉ ሁኔታ ብዙ ችግሮች የሚያስከትል እንደሆነ ቢታመንም፣ ወያኔ በአገርና በሕዝብ ላይ ትውልድና ታሪክ ይቅር ከማልለው ወንጀል ራሱን «ነፃ« ሊያደርግበት የሚችለው ብቸኛው መንገድ ትግራይን መገንጠል ስለሆነ፣ አያደርገውም ለማለት አያስደፍርም። ይህን ሲያደርግ ግን ከሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ ሊደርስበት እንደሚችል መገመት ቢቻልም፣ ሕዝቡ ይህ አይቀሬ መሆኑን ተረድቶ ካሁኑ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን መቆም ካልቻለ በኋላ ላይ የሚያሰማው ተቃውሞ መርዶ ነጋሪ ከመሆን ያለፈ ፋይዳ ይኖረዋል አይባልም። ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ለትግራይ ሕዝብ ሲያየው የነበረው ሆደ ሠፊነትና የአብሮነት ስሜት ጨርሶ ሳይሚጠጥና እኛ እና እነሱ የሚለው ልዩነት ሳይሰፋ፤ለተዘረጋለት የአብሮነት ጥሪ ምላሹን በእጥፍ ለመመለስ ከመዘጋጀት አልፎ በተግባር ሊያረጋግጥ ካልቻለ፣ ሊከተል የሚችለውን አደጋ የቱን ያህል የከፋ ሊሆን እንደሚችል መገመት ያዳግታል  አይባልም።

ዛሬ የወያኔ ጩኸቱን ቀሙኝ ዓይነት፣ ለ17 ዓመት ታግዬ፣ ሙቼና ደክሜ የጨበጥኩትን ሥልጣን ልነጠቅ አይገባም ብሎ የሚያሰማን ሮሮ ግብ፣ ፈጽሞ ከሥልጣን አልወርድም የማለት ከዕብሪት ዘሎ የእብደት ዋይታና ድንፋታ፣ ተያይዘን እንጥፋለን እንጂ፤የሚታሰብ አይደለም እያለን ነው። ይህ የባለጌ ድፍረት ነው።የቀረበልን ምርጫ ባርነት ወይም ሞት ነው። ስለሆነም ለነፃነት መሞት ለእኛ ኢትዮጵያውያን ብርቅና አዲስ ነገር አይደለም። አንድነታችንና ነፃነታችን ፀንቶን አንጸባርቀው የኖሩት ከባርነት ነፃነትን የመረጥ ብቻ ሳይሆን፣ የነፃነትን ክቡር ዋጋ በሚገባ የምናውቅ በመሆአችን ነው። በመሆኑም ለዘላለም በባርነት ከመኖር፣ ላንድ ቀን ጀንመበር በነፃነት መቆም ታላቅ ዋጋና ክብር ያለው መሆኑን ስለምረዳ የነፃነቱ ጎዳና ምርጫችን ነው።

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ህብረት ከወደቀችበት ትነሳለች!

ውድ እናት ሀገር እትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!